የማኒቶባ የክልል
ሪፖርት ካርድ

መረጃ

# ለወላጆች

ከ 1 ኛ እስከ 8 ኛ ክፍሎች



Manitoba

*የማኒቶባ ትምርት ለሁሉም የትምርት ክፍፍሎች፡ በ2013/2014 የትምርት ዘመን የግድ መጠቀም ያለባቸው የክልል ሪፖርት ካርድ መጠቀም ጀምሯል፡፡*

# አጠቃላይ

## ለምንድነው አዲስ የሪፖርት ካርድ የተፈለገው?

የማኒቶባ መንግስት በማኒቶባ ውስጥ ያለው የትምህርት ጥራት ለማሻሻልና በተማሪዎች፣ ኣስተማሪዎቻቸውና ወላጆቻቸው መካከል ጠንካራ ግኑኝነት ለመገንባት አዲስ የሪፖርት ካርድ መጠቀም ጀምሯል፡፡

ቀደም ሲል፣ የሪፖርት ካርዶች በያንዳንዱ የትምርትቤት ክፍፍል እንዲሁም፣ በተወሰኑ ኣጋጣሚዎች፣ በአንድ ዓይነት ክፍፍል የሚገኙ ትምህርት ቤቶች የተለያዩ ነበሩ፡፡ ይኸ አዲስ የክልል ሪፖርት ካርድ፡ ወላጆች ልጆቻቸው ምን ያክል በጥሩ ሁኔታ እየተማሩ ናቸው፣ የመማር ሂደት እንዲሻሻል ምን ዓይነት እርምጃዎች ናቸው እገዛ የሚያደርጉት በሚሉት ጉዳዮች ላይ የማይለወጥና፣ ግልጽ መረጃ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳ እዩ፡፡

## የሪፖርት ካርዱ ለመረዳት ቀላል ይሆናል ወይ?

የሪፖርት ካርዱ በቀላል ቋንቋ የተፃፈ ነው፡፡ የልጅዎ ጠንካራ ጎን እንዲሁም ልጅዎ ምን ላይ ነው እገዛ የሚያስፈልገው ይነግርዎታል፡፡ ስለዚህ የሪፖርት ካርድ ጥያቄዎች ካልዎ፣ የልጅዎን

ኣስተማሪ ማነጋገር ይችላሉ፡፡

## የሪፖርት ካርዱ ለሁሉም የክፍል ደረጃዎች አንድ ዓይነት ነውን?

ሶስት ዓይነት የሪፖርት ካርድ ቅርጾች ኣሉ፡፡ ኣንዱ ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል፣ አንዱ ከ7ኛ እስከ 8ኛ ክፍል እንዲሁም ሌላው ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ናቸው፡፡

## በሪፖርት ካርዱ ላይ ያስተማሪ ኣስተያየቶች ይኖራሉን?

አዎን፡፡ ኣስተማሪዎች ልጅዎ በትምርትቤት ስለሚያሳየው ውጤትና ፀባይ አስተያየታቸውን ይጽፋሉ፡፡ እነዚህ አስተያየቶች ልጅዎ እንዴት እየሄደ ነው እንዲሁም እንዴት የልጅዎ የመማር ሂደት ማገዝ ይቻላል ለመረዳት ያግዝዎታል፡፡

## ልጄ እንዴት ነው የሚገመገው?

የትምርት ስኬት ውጤቶች ተማሪዎች የስርዓተ-ትምርት የመማር ዓላማዎች ምን ያክል በጥሩ ሁኔታ እያሳኩ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይኸ ደግሞ መስፈርት-ያጣቀሰ የውጤት ኣሰጣጥ በመባል ይታወቃል፡፡ የትምርት ስኬት ውጤቶች፡ ልጅዎ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በማነጻጸር እንዴት እየሰራ ነው በሚል የተመሰረቱ ኣይደሉም፡፡ አስተሳሰብ፣ ጥረትና ፀባይ የመሳሰሉ ምክንያቶች ከትምርት ስኬት ተነጥለው ሪፖርት ይደረጋሉ፡፡ እነዚህ ምክንያቶች በትምርት ስኬት ብሎም ውጤቶች ላይ ተፅኖ የሚያሳድሩ መሆናቸው ግልፅ ሆኖ እንዳለ፣ በተናጠል ሪፖርት መደረጋቸው ለወላጆች የልጃቸው ጠንካራ ጎኖችና ማሻሻል ስለ ሚቻልባቸው ዙርያዎች የበለጠ መረጃ ይሰጣል፡፡

ኣስተማሪዎች ተማሪዎች ያላቸው ክህሎቶች እና አንድን የትምርት ዓይነት የመረዳት ችሎታ እንዲያሳዩ በርካታ መንገዶች ያዘጋጅሏቸዋል፡፡ የስኬት ውጤቶች ባጠቃላይ የልጅዎ በጣም የቅርብ ግዜ እንዲሁም የማይለወጥ የትምርት ስኬት ያንፀባርቃሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ይህ ማለት ደግሞ በአንድ ሴመስተር መጀመርያ ላይ በተሰጠ የቤት ስራ ላይ የተገኘ ዝቅተኛ ውጤት፡ በሴመስተሩ መጨረሻ የልጆዎ ውጤት በሚገመገምበት ወቅት፡ እሱ/ሷ በዛ ዙርያ የበለጠ መረዳት ወይም ክህሎት ካገኘ/ኘች ግምት ውስጥ ላይገባ ይችላል፡፡



## ልጄ በአንድ ክፍል ሊወድቅ (ሊደግም) ይችላልን ?

አዎን፡፡ አንድ ተማሪን የማሳለፍና የመጣል ውሳኔ፡ በሌሎች ጉዳዮች መካከል፣ የተማሪው ለውጥና ዕድገትን የሚገልጽ ማስረጃን በመጨመር፡ የተለያዩ ምክንያቶች ጠንቃቃ ግምገማ ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ የማሳለፍ ውሳኔዎች በትምርት ቤቱ ርእሰ-መምህር ነው የሚፈጸሙት፤ እሱም ከአስተማሪዎች፣ ወላጆችና ሌሎች

ሞያተኞች ጋር በተገቢው መንገድ የሚማከር ነው፡፡ አንድ ተማሪን የማሳለፍና የመጣል ውሳኔዎች ሁሌ የተማሪው ጥቅሞች በሚያስከብሩ መልካቸው ናቸው የሚሰጡት፡፡

## የሪፖርት ካርዱ መቼ ነው ወደ ቤት የሚላከው?

የሪፖርት ካርድ ወደ ቤት የሚላኩት በመፀው፣ በፀደይና በትምርት ዘመን መጨረሻ ነው፡፡

## በሌሎች ግዜያቶች ካስተማሪዎች መረጃ ኣገኛለውን?

አዎን፡፡ ሪፖርት ካርዱ ከወላጆች ጋር የሚያገናኝ ኣንዱ መንገድ ብቻ ነው፡፡ ሌሎች ዘዴዎች፣ ስልክ መደወል፣ ስርዓት ያልተከተለ የዕድገት ሪፖርቶች፣ የወላጅ-ኣስተማሪ ስብሰባዎች፣ በተማሪ-የሚመሩ ጉባኤዎች፣ እንዲሁም የትምርት ቤት መፅሄቶች ያጠቃልላሉ፡፡

## የልጄ የትምርት ቤት ውጤት ካሳሰበኝ ምን ማድረግ ኣለብኝ?

የልጅዎን አስተማሪ ያነጋግሩ፡፡ ለልጅዎ ኣስቸጋሪ በሆኑባቸው የትምርት ዙርያዎች ዝርዝር ማዘጋጀት ኣጋዥ ይሆናል፡፡ ልጅዎ ስኬታማ እንዲሆን እንዴት በጋራ መስራት እንደሚችሉ አስተማሪውን ያነጋግሩ፡፡

*በዚህ ሰነድ ላይ፣ ወላጆች የሚል ቃል ለወላጆች ወይም አሳዳጊዎች የሚገልጽ ነው፡፡*

# የተማሪ ፕሮግራም አወጣጥ

*የልጅዎ ፕሮግራም አወጣጥ*፡ ልጅዎ በክፍል-ደረጃ የተመረኮዘ ስርዓተ-ትምርት ይከተላል/ትከተላለች ወይስ ኣይከተልም/አትከተልም፣ ወይም ለመማር የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት ነገሮች በበለጠ ለሟሟላት በልዩ ሁኔታ የተነደፈ ሌላ የፕሮግራም አወጣጥን ይገልጻል፡፡



ልጅዎ በአንድ የትምርት ዓይነት በክፍል- ደረጃ የተመሮኮዘ ስርዓተ-ትምርት እየተከተለ ካልሆነ፣ የሪፖርት ካርዱ የሚከተሉት ሶስት የፕሮግራም አወጣጥ ዓይነቶች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

## 1. የIEP ፕሮግራም አወጣጥ

"IEP" የግል የትምርት ዕቅድን ያመለክታል፡፡ አንድ በትምርት ዓይነት የክፍል-ደረጃ የመማር ዓላማዎች ማሟላት የማይጠበቅበት ተማሪ፡ የግል የመማር ዓላማዎች የሚገልፅ የግል የትምርት ዕቅድ ይኖረዋል፡፡ ይህ ተማሪ በሪፖርት ካርዱ ላይ የሚያገኛቸው ውጤቶች፡ ከተጠቀሰው ተማሪ ጋር የሚዛመዱ የመማር ዓላማዎችን ያመለክታሉ፣ እንዲሁም እነዚያ ዓላማዎች በተማሪው ዕቅድ ላይ በግልፅ ተዘርዝሯል፡፡

የ"IEP" አመልካች አንድ ተማሪ በአንድ የትምርት ዓይነት ካለው የክፍል ደረጃ በላይ ግምት የሚሰጠው ስራ እየሰራ ካለ፡ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፣ እንዲሁም IEP ይህን በሚመለከት በቦታው እንዳለ ያሳያል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው፣ ተማሪው በሪፖርት ካርዱ ላይ የሚያገኛቸው ውጤቶች ዕቅዱ ላይ በተዘረዘሩት መሰረት የተማሪው የመማር ዓላማዎችን ያመለክታሉ፡፡

## 2. EAL የፕሮግራም አወጣጥ

"EAL" የእንግሊዘኛ እንደ ተጨማሪ ቋንቋ የፕሮግራም አወጣጥን ይገልጻል፡፡ አንድ ተማሪ በመጀመርያ የእንሊዘኛ እንደ ተጨማሪ ቋንቋ የመማር መድረኮች ላይ፡ የትምርት ዓይነቱን የሚመለከት የእንሊዘኛ ቋንቋ በመማር ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ ተማሪ በሪፖርት ካርዱ ላይ የሚያገኛቸው ውጤቶች፡ ከተጠቀሰው ተማሪ የቋንቋ ችሎታ ደረጃ ጋር የሚዛመድ፡ በቋንቋና የትምርት ዓይነት የመማር ዓላማዎች መካከል ያለው መመዛዘን ላይ የተመሮኮዘ ነው፡፡

## 3. L የፕሮግራም አወጣጥ

"L" የፈረንሳይኛ የመጻፍና ማንበብ መቻል የፕርግራም አወጣጥን ያመለክታል፣ እንዲሁም ለፈረንሳይኛ ፕሮግራም ብቻ ይመለከታል፡፡ የክልል ስርዓተ-ትምርቱ ስኬታማ በሆነ መንገድ ለመከተል፣ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ችሎታው ለማሳደግ ተጨማሪ እገዛ የሚያስፈልገው ተማሪ፡ በትምርት ዓይነት በመርኮዝ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ክህሎቶች በመማር ላይ ሊያተኩር ይችላል፡፡ ይህ ተማሪ በሪፖርት ካርዱ ላይ የሚያገኛቸው ውጤቶች፡ ከተጠቀሰው ተማሪ የቋንቋ ችሎታ ደረጃ ጋር የሚስማሙ፡ በቋንቋና የትምርት ዓይነት የመማር ዓላማዎች ያለ መመዛን ላይ የሚመረኮዝ ነው፡፡ እነዚያ ዓላማዎች በተማሪው በፈረንሳይኛ የመጻፍና የማንበብ የትምርት ዕቅድ ላይ በግልጽ ተዘርዝሯል፡፡

ታች ከተገለጸው የ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍሎች የሪፖርት ካርድ፣ ፕሮግራም አወጣጡ በ"x." ተመልክቶ ሊያዩ ይችላሉ፡፡ ምንም የተመለከተ ነገር ከሌለ፣ ልጅዎ በክፍል-ደረጃ የተመረኮዘ ስርዓተ-ትምርት የመማር ዓላማዎች እየተከተለ ነው ማለት ነው፡፡

| **Mathematics** | **Teacher:** | | |
|---|---|---|---|
| ☐ **EAL** ☒ **IEP** | Term 1 | Term 2 | Final |
| Knowledge and understanding | | | |
| Mental math and estimation | | | |
| Problem solving | | | |
| Comments: | | | |

ፕሮግራራም አደራረግ እዚህ ላይ ተመልክቷል፡፡

*መለማመድ የሚለው ቃል በማስተማር ሂደት፣ ማተሪያሎች፣ የቤት ስራ ወይም የተማሪ ምርቶች ወይም አንድ ተማሪ የሚጠበቁበትን የመማር ውጤቶች ለማሳካት የሚረዱ የተማሪ ምርቶች በሚመለከት የተደረገ ለውጥን ያመለክታል፡፡*

# የክልል የሚጠበቁ ነገሮችን የሚያመለክት የትምርት ስኬት

## ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል

ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍሎች፣ የሚከተለው *ከ 1 እስከ 4 የሆነ የውጤት መለኪያ*፡ የልጅዎ የያንዳንዱ የትምርት ዓይነት ምድብ (ከታች የተገለፀው) በያንዳንዱ የትምርት ዓይነት ላይ፡ ትምርት-ነክ ስኬትን ለመግለጽ በሪፖርት ካርድ ላይ እንጠቀምበታለን፡፡

| Grade Scale | | Academic Achievement of Provincial Expectations |
|---|---|---|
| **4** | | Very good to excellent understanding and application of concepts and skills |
| **3** | | Good understanding and application of concepts and skills |
| **2** | | Basic understanding and application of concepts and skills |
| **1** | | Limited understanding and application of concepts and skills; see teacher comments |
| **ND** | | Does **N**ot yet **D**emonstrate the required understanding and application of concepts and skills; see teacher comments |
| **Additional Codes** | **NA** | **N**ot **A**pplicable |
| | **IN** | **In**complete: not enough evidence available to determine a grade at this time |

| One of the following codes is used if the expectations for a student are different from the grade-level curriculum in a subject. | |
|---|---|
| **EAL** (**E**nglish as an **A**dditional **L**anguage) | Achievement is based on expectations that focus on English language learning. |
| **IEP** (**I**ndividual **E**ducation **P**lan) | Achievement is based on expectations that reflect special learning needs. |

ከታች ለምሳሌ የቀረበ የ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍሎች ሪፖርት ካርድ፡ የዚህ የውጤት መለኪያ ለአንድ በ2ኛ ሴመስተር የEAL ፕሮግራም አደራረግ ያለው ሂሳብ የትምርት ዓይነት እየወሰደ ያለ ተማሪ ነው፡፡ እያንዳንዱ የተጠቀሰው የትምርት ዓይነት ከመለኪያው የራሱ የሆነ ውጤት እንደሚሰጠው ያስተውሉ፡፡

| **Mathematics** | **Teacher:** | | |
|---|---|---|---|
| ☒ **EAL** ☐ **IEP** | **Term 1** | **Term 2** | **Final** |
| Knowledge and understanding | 3 | 2 | |
| Mental math and estimation | 2 | 3 | |
| Problem solving | 3 | 3 | |
| Comments: | | | |

ፕሮግራም አደራረግ

የትምርት ዓይነት ምድብ

አሁን ያለው ሴመስተር/ የትምርት ክፍለ-ዓመት

## የትምርት ዓይነት ምድቦች

የትምርት ዓይነት ምድቦች፡ ልጅዎ በያንዳንዱ የትምርት ዓይነት በትምርት ቤት የሚማራቸው የዕውቀት ዘርፍና ክህሎት ናቸው፡፡ ስለልጅዎ ትምርት በበለጠ ያስረድዎታል፡፡ የትምርት ዓይነት ምድቦቹ፡ ያ “ምን” የሚለው ከተማሪ ጥያቄዎች አንድ አካል ሆኖ፡ የተማሪ የመማር ሂደት ለመግለጽ ይረዳል፡፡ የማስተማር፣ በሁሉም የትምርት ዓይነት ዘርፎች የመማርና የመርመር ሂደት አካል እንዲሆኑ ተብለው የተነደፉ ናቸው፣ የተወሰኑ ርዕሶች ሲማሩ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውሉ አይደሉም፡፡



# የክልል የሚጠበቁ ነገሮችን የሚያመለክት የትምርት ስኬት

## 7ኛና 8ኛ ክፍሎች

በ7ኛና 8ኛ ክፍሎች፣ *ከ 1 እስከ 4 የሆነው የውጤት መለኪያ* በተጨማሪ፣ የመቶኛ መለኪያ አጠቃላይ የትምርት ዓይነት ውጤት ለመስጠት ያገለግላል፡፡ ይህ ወደ የሁለተኛ ደረጃ ሪፖርት ካርዶች ማሸጋገር ላይ ያነጣጠር ሲሆን፡ አጠቃላይ የትምርት ዓይነት ውጤቶች፡ የመቶኛ መለኪያ በመጠቀም ለያንዳንዱ የትምርት ዓይነት ይሰጣል ምክንያቱም የተማሪዎች ስኬት ለማጠቃለል ተማሪዎች ወደ መመረቂያቸው የሚታሰብ ውጤቶች ስለሚያከማቹ፡፡ ይህ የሚከተለው ሰንጠረጅ ሁለት የውጤት መለኪያዎች እርስ በራሳቸው እንዴት ይዛመዳሉ ያሳያል፡፡



| Academic Achievement of Provincial Expectations | |
|---|---|
| **Grade Scale** | **Descriptor** |
| **4**<br>**80% to 100%** | Very good to excellent understanding and application of concepts and skills |
| **3**<br>**70% to 79%** | Good understanding and application of concepts and skills |
| **2**<br>**60% to 69%** | Basic understanding and application of concepts and skills |
| **1**<br>**50% to 59%** | Limited understanding and application of concepts and skills; see teacher comments |
| **ND**<br>**Less than 50%** | Does **N**ot yet **D**emonstrate the required understanding and application of concepts and skills; see teacher comments |

የሚከተለው ምሳሌ የ7ኛ እስከ 8ኛ የሪፖርት ካርድ ሲሆን፡ የአድድ ከ2ኛ ሴመስተር በክፍል ደረጃ የተመረኮዘ መደበኛ የትምርት ዓይነት የፕሮግራም አወጣጥ ላይ፡ የሳይንስ ትምርት የሚወስድ ተማሪን ያሳያል፣ እንዲሁም በትምርት ዓይነቱ ውስጥ የሚገኙ ሶስቱ የትምርት ዓይነት ምድቦችን ያሳያል፡፡

| **Science** | | | | Teacher: | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ☐ **EAL** ☐ **IEP** | | | | ☐ **IEP** | | | |
| **Academic Achievement** | **Term 1** | **Term 2** | **Final** | **Learning Behaviours** | **Term 1** | **Term 2** | **Term 3** |
| Knowledge and understanding | 3 | 2 | | Personal management skills | U | U | |
| Scientific inquiry process | 3 | 3 | | Active participation in learning | C | U | |
| Design process and problem solving | 4 | 4 | | Social responsibility | S | C | |
| Overall grade | 78% | 70% | % | | | | |
| Comments: | | | | | | | |

እነዚህ የትምርት ዓይነት ምድቦቹ ናቸው፡፡

እነዚህ የመማር ፀባዮቹ ናቸው፡፡

# የመማር ፀባዮች

ትምርት-ነክ ስኬት ሪፖርት ከማድረግ በተጨማሪ፣ የሪፖርት ካርዶች ልጅዎ ክፍል ውስጥ የሚያሳየው ጥረትና አመለካከትን ያሳያል፣ ቀደም ሲልና ከታች እንደተገለጹትና እንደተጠቀሱት ምሳሌዎች እንደምናየው፣ “የመማር ፀባዮች” ከሚለው ስር ተገልጿል፡፡

ከ1ኛ  እስከ 6ኛ ክፍሎች፤ የመማር ፀባዮች በልጅዎ ሪፖርት ካርድ ላይ አንዴ ይሰፍራሉ (ለሁሉም የትርት ዓይነቶች)፡፡ ከ7ኛ እስከ 8ኛ ክፍሎች፣ ለያንዳንዱ ልጅዎ የሚወስደው የትምርት ዓይነት ሪፖርት ይሰፍራል፡፡ ልጅዎ ከመማር ፀባዮች ጋር የሚዛመዱ ዓላማዎች ያላቸው የግል የትምርት ዕቅድ ካለው፣ IEP ይገለጻል፡፡

| Learning Behaviours | |
|---|---|
| **Scale**<br>**C**: Consistently – almost all or all of the time<br>**U**: Usually – more than half of the time<br>**S**: Sometimes – less than half of the time<br>**R**: Rarely – almost never or never | |
| **Personal management skills** | Uses class time effectively; works independently; completes homework and assignments on time |
| **Active participation in learning** | Participates in class activities; self assesses; sets learning goals |
| **Social responsibility** | Works well with others; resolves conflicts appropriately; respects self, others and the environment; contributes in a positive way to communities |

በፍሬንች ኢመርሽን ፕሮግራም ተሳታፊ ለሆኑ ተማሪዎች፣ የተማሪዎች የፈረንሳይኛ ቋንቋ አጠቃቃም ተግባርን በተመለከተ የመማር ጸባይ አለ፡፡



የመማር ፀባዮች በቀጥታ በተማሪዎች ውጤቶች ላይ የሚካተቱ አይደሉም፣ ሆኖም ግን፣ በትምርት-ነክ ስኬታቸው ላይ ጫና ሊያሳርፉ ይችላሉ፡፡ ጠቃሚ የመማር ፀባዮች ማሳደግ፡ በትምርት ቤትም ሆነ ውጭ በህይወታቸው ላይ ለውጥ እያመጡ በምሄዱበት ወቅት፡ ለመጪው ግዜ ለተማሪዎች ለውጥ ሊያመጣላቸው ይችላል፡፡ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው ከሰሩ፣ ተነሳሽነት ካሳዩ፣ እንዲሁም የመማርያ ክፍል ክብሮችን ካከበሩ፣ እነዚህ ክህሎቶች በተለያዩ ሌሎች የህይወታቸው ዘርፎች ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ፡፡

# ለተጨማሪ መረጃ

ለተጨማሪ መረጃ የማኒቶባ ትምርት ድረገጽን ይጎብኙ፡

- ልጅዎ **በተለያዩ የትምርት ዓይነት ዙርያዎች** ላይ ምን እየተማረ እንደሆነ ለመረዳት፡-
  www.edu.gov.mb.ca/k12/cur/parents/ (የእንግሊዘኛ ፕሮግራም)
  www.edu.gov.mb.ca/k12/cur/parents/fr_imm/ (የፈረንሳይኛ ኢመርሽን (Immersion) ፕሮግራም)
  www.edu.gov.mb.ca/m12/progetu/parents/ (*የፈረንሳይኛ ፕሮግራም*)
- **ተማሪን ለመመርመር** የተዘጋጁ ፖሊሲዎችና መመርያዎች፡-
  www.edu.gov.mb.ca/k12/assess/
- **የክልል ሪፖርት ካርድ**፡-
  www.edu.gov.mb.ca/k12/assess/report_cards/index.html

# የምትጨምሩት ነገር በደስታ እንቀበላለን

ወላጅ ወይም ኣሳዳጊ፣ አስተማሪ፣ ተማሪ ወይም ፍልጎት ያለው የማህበረሰብ አባልም ይሁኑ፣ ለዚህ አዲስ የሪፖርት ካርድ ያልዎት ምላሽ አስፈላጊ ነው፡፡ ባጠቃላይ፣ ሪፖርት ካርድ ግልጽና መረጃ ሰጭ ሆኖ አገኙት ወይ? አሁንም ቢሆን መሻሻል ያለባቸው የሪፖርት ካርዱ ክፍሎች አሉን?

አስተያየትዎ ማቅረብ ከፈለጉ፣ እባክዎን ከታች ወደ ተገለጸው አድራሻ በፖስታ ይላኩት ወይም የተመለከተው የኢንተርነት ድረ-ገፅ በመጎብኘት የኦንላይን የምላሽ መስጫ ቅፅ ሞልተው ይላኩ፡፡

| ምላሽ በፖስታ ይላኩ | ምላሽ በኦንላይን |
|---|---|
| *Provincial Report Card Feedback*<br>Manitoba Education<br>1567 Dublin Avenue<br>Winnipeg MB  R3E 3J5 | www.edu.gov.mb.ca/k12/assess/report_cards/feedback.html |

*ጥያቄ ካቀረቡ በሌላ ዓይነት ቅርጾች/መልኮች ሊያገኙ ይችላሉ፡፡*